ትምህርት 20

1. የድሮ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ስለተዉ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳን ያቀደውን ዕቅድ ትቷል?

ሀ- አልተወም።

2. አብዛኛዎቹ የድሮ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ስላልፈለጉ እግዚአብሔር አዳኝ በእርሱ ዘር በኩል ለመላክ የመረጠው ሰው ማን ነበር?

ሀ- አብራም።

3. እግዚአብሔር አብራምን የመረጠው፥ አብራም ኃጢአት ስላልሠራ ነበር?

ሀ- አልነበረም አብራም ኃጢአተኛ ሆኖ ነበር የተወለደው።

4. እግዚአብሔር አብራምን ለምን መረጠው?

ሀ- አብራም ለኃጢአቱ የሚገባው ቅጣት ሞት እንደሆነ ስላመነ።

ለ- አብራም ከኃጢአቱ ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ስላመነ።

ሐ- አብራም እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ ስላመነ።

5. አብራም ሦራን አገባ አብራምና ሦራ ስንት ልጆች ነበሯቸው?

ሀ- ምንም ልጅ አልነበራቸውም።

6. አብራምና ሦራ ልጅ ያልወለዱት ለምንድን ነው?

ሀ- ሦራ መካን ስለ ነበረች።

7. እግዚአብሔር አብራም ምን እንዲያደርግ ነገረው?

ሀ- እግዚአብሔር አብራም አገሩን ለቅቆ እርሱ ወደሚያሳየው አገር እንዲሄድ ነገረው።

8. እግዚአብሔር ለአብራም የተናገረው በድምፁ ነበር። እግዚአብሔር ለእኛ ዛሬ የሚናገረው እንዴት ነው?

*ሀ- ዛሬ በአብዛኛው እግዚአብሔር የሚናገረን በመጽሐፉ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ነው።*

9. እግዚአብሔር ለአብራም የገባለት የተስፋ ቃል ምን ነበር?

*ሀ- አንደኛ እግዚአብሔር አብራም ታላቅ ሕዝብ የሚሆኑ ብዙ ዘሮች ንደሚኖሩት ቃል ገባ።*

*ለ- ሁለተኛ እግዚአብሔር አብራምን እንደሚባርከው ቃል ገባ።*

*ሐ- ሦስተኛ እግዚአብሔር አብራምን የሚባርኩትን እንደሚባርክ የሚረግሙትን እንደሚረግም ቃል ገባ።*

*መ- አራተኛ እግዚአብሔር ከአብራም ዘር በሆነ በአንድ ሰው አማካይነት ሰውን ሁሉ እንደሚባርክ ቃል ገባ።*

10. ከአብራም ዘር የሆነውና ሰዎች ሁሉ በእርሱ አማካይነት የሚባረኩበት ማን ነው?

*ሀ- አዳኙ።*

11. አዳኙ የሚመጣው ምን ለማድረግ ነው?

*ሀ- አዳኙ የሚመጣው ያኃጢአትን ኃይል ለማሸነፍ ነው።*

*ለ- አዳኙ የሚመጣው የሞትን ኃይል ለማሸነፍ ነው።*

*ሐ- አዳኙ የሚመጣው የሰይጣንን ኃይል ለማሸነፍ ነው።*

*መ- አዳኙ የሚመጣው እግዚአብሔርና ሰው ዳግመኛ ኅብረትን እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው።*

12. አብራም በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ያምኖን ነበር?

*ሀ- አዎን።*

13. እግዚአብሔር ለአብራም ቃል ከገባ በኋላ አብራም ምን አደረገ?
ሀ- አብራም ይኖርበት የነበረውን አገር ለቅቆ እግዚአብሔርን በመከተል እርሱ ወደሚመራው አገር ሄደ።

14. እግዚአብሔር አብራምን የመራው ወዴት ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር አብራምን ከነዓን ወደ ተባለ አዲስ አገር መራው።

- ሎጥ ማን እንደ ነበረ ታስታውሳላችሁ?

- ሎጥ ከአብራም ጋር ወደ ከነዓን የሄደ፥ የአብርሃም የወንድሙ ልጅ ነበር።

- አንድ ቀን በሎጥና በአብራም መካከል ችግር ተፈጠረ።

ዘፍጥረት 13፡5-7

5- ከአብራም ጋር አብሮት ይጓዝ የነበረው ሎጥ በጎች፣ ከብቶችና ድንኳኖች ነበሩት።
6- ሆኖም ሁለቱ አንድ ላይ ሲኖሩ ስፍራው አልበቃቸውም፣ ንብረታቸው እጅግ ብዙ ስለ ነበር፣ አብረው መኖር አልቻሉም።
7- ይህም በመሆኑ በአብራምና በሎጥ እረኞች መካከል ጠብ ተፈጠረ።

- በአብራምና በሎጥ መካከል የተፈጠረው ችግር ምን ነበር?

- አብራም ብዙ በጎችና ከብቶች ነበሩት።

- ሎጥም ደግሞ ብዙ በጎችና ከብቶች ነበሩት።

- ሎጥና አብራም ብዙ በጎችና ከብቶች ስለነበሯቸው ከብቶቻቸውን ሁሉ ለመመገብ በቂ ሣር አልነበረም።

- አብራም ችግሩን ለመፍታት ምን አሰበ?

ዘፍጥረት 13፡8-9

8- አብራምም ሎጥን እንዲህ አለው፤ «እኛ ወንድማማቾች ነንና፣ በአንተና በእኔ፣ ወይም በእረኞቻችን መካከል ጠብ ሊኖር አይገባም።

9- ይኸው እንደምታየው አገሩ ሰፊ ነው። ብንለያይ ይሻላል። አንተ ግራውን ብትመርጥ፣ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተ ቀኙን ብትመርጥ፣ እኔ ወደ ግራ አመራለሁ።

- አብራም እርሱና ሎጥ መለያየት እንዳለባቸው አሰበ።

- አብራም ሎጥ የት መኖር እንደሚፈልግ እንዲመርጥ ዕድሉን ሰጠው።

- ሎጥ ቆላ ለመኖር ከመረጠ አብራም ደጋ ለመኖር አሰበ።

- ሎጥ ደጋ ለመኖር ከመረጠ አብራም ቆላ ለመኖር አሰበ።

- ሎጥ ምን እንደ መረጠ እናንብብ።

ዘፍጥረት 13፡10-11

10- ሎጥ ዓይኑን አቅንቶ ሲመለከት፣ የዮርዳኖስ ረባዳ ሜዳ እንደ እግዚአብሔር ገነት፣ በዞዐር አቅጣጫ እንዳለው እንደ ግብፅ ምድር ውኃማ ቦታ ሆኖ አገኘው።

11- ሎጥ የዮርዳኖስን ረባዳ ሜዳ በሙሉ መርጦ ወደ ምሥራቅ አመራ፤ ሁለቱ ሰዎች በዚሁ ተለያዩ።

- ሎጥ በቆላማ ስፍራ ለመኖር መረጠ።

- ሎጥ በቆላማ ስፍራ ለመኖር የፈለገው ለምን ነበር?

- በዚያ በጎቹንና ከብቶቹን ለመመገብ በቂ ሣር ስለ ነበረ ነው።

- ሎጥ ስለ ሣር ብቻ ያስብ ነበር።

- ሎጥ ለብዙዎቹ በጐቹና ከብቶቹ ብቻ ያስብ ነበር።
- ሎጥ ለሀብት ብቻ ያስብ ነበር።

- ሎጥ በቆላማ ስፍራ ለመኖር መምረጡ ስሕተት ነበር።
- ሎጥ የተሳሳተ ምርጫ ያደረገው እንዴት ነው?

- ሎጥ የተሳሳተው ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔርን ስላልጠየቀ ነው።
- ሎጥ እግዚአብሔርን መስማት ስላልፈለገ ነው።

- ቃየን እግዚአብሔርን መስማት ባለመፈለጉ ወንድሙን አቤልን ገደለው።

- የቃየን ዘሮች እግዚአብሔርን መስማት አልፈለጉም።

- ሁሉም የቃየን ዘሮች በጥፋት ውኃ ሞቱ።

- እግዚአብሔርን መስማት ካልፈለግን ምን ይደርስብናል?
- እግዚአብሔርን መስማት ካልፈለግን እኛም ደግሞ እንሞታለን።

- እግዚአብሔርን መስማት ካልፈለግን እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለአጋንንቱ ወዳዘጋጀው ወደ ዘላለሙ የእሳት ባሕር እንሄዳለን።

- ብዙ በግና ከብት ወይም ሀብት ከዘላለሙ የእሳት ባሕር ያድነናል?
- አያድነንም።

- ሎጥ እግዚአብሔርን መስማት ባለመፈለጉ ወደ ቆላማ ስፍራ ሄደ።

ዘፍጥረት 13፡12-13

12- አብራም መኖሪያውን በከነዓን ምድር አደረገ፣ ሎጥ ግን በረባዳው ሜዳ ውስጥ ባሉት ከተሞች መካከል በሰዶም አቅራቢያ ድንኳኑን ተከለ።

13- የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጥአን ነበሩ።

- በቆላማው ስፍራ ሁለት ከተሞች ነበሩ።
- የከተሞቹም ስም ሰዶምና ገሞራ ነበር።

- የሰዶምና የገሞራ ሕዝቦች በእግዚአብሔር አያምኑም ነበር።
- የሰዶምና የገሞራ ሰዎች በጣም ክፉዎች ነበሩ።

- እግዚአብሔር የሰዶምንና የገሞራን ሕዝቦች ክፋት አይቷል?
- አዎን።

- የምናስበውን ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር መደበቅ እንችላለን?
- አንችልም።

- የምንናገረውን ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር መደበቅ እንችላለን?
- አንችልም?

- የምናደርገውን ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር መደበቅ እንችላለን።

- አንችልም።

- ሎጥ ወደ ቆላማው ስፍራ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር ለአብራም ምን አለው?

ዘፍጥረት 13፥14-15 & 17

14- ሎጥ ከተለየው በኋላ እግዚአብሔር አብራምን እንዲህ አለው፣ «ካለህበት ስፍራ ቀና ብለህ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ተመልከት፤

15- ዓይንህ የሚያየውን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጣለሁ።

17- እንግዲህ ምድሪቱን ስለምሰጥህ ተነሣ፣ በርዝመቷም በስፋቷም ተመላለስባት።»

- እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር በሙሉ ለአብራም እንደሚሰጥ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ለአብራም በተጨማሪ እንዲህ አለው፡-

ዘፍጥረት 15፥5-6

5- ወደ ውጭም አውጥቶ፣ «ቀና ብለህ ወደ ሰማይ ተመልከት እስቲ መቁጠር ከቻልህ ክዋክብቱን ቁጠራቸው፤ ዘርህም እንዲሁ ይበዛል» አለው።

6- አብራም እግዚአብሔርን አመነ፣ እርሱም ጽድቅ አድርጎ ቆጠረለት።

- ደግሞም እግዚአብሔር አብራም እንደ ክዋክብት የበዙ ዘሮች እንደሚኖሩት ነገረው።

- ክዋክብት ስንት ናቸው?
- ማንም ሰው ቆጥሮ ሊጨርስ አይችልም።

- አብራም ምንም ልጅ ባይኖረውም፥ እንደ ከዋክብት የበዙ ልጆች እንደሚኖሩት እግዚአብሔር ነገረው።

- አብራም ምንም ልጅ ባይኖረውም፥ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል አመነ?
- አዎን።

- አብራም እግዚአብሔር አንድ ቀን ልጅ እንደሚሰጠው አመነ።

- በተጨማሪም አብራም ከእርሱ ዘር አንዱ፥ እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን የሚልከው አዳኝ እንድሚሆን አመነ።

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ያለውን እንመልከት፡-

ዘፍጥረት 15፡13-16

13- እግዚአብሔር እንዲህ አለው፤ «ዘርህ በባዕድ አገር ስደተኛ እንደሚሆን በእርግጥ እወቅ፤ አራት መቶ ዓመትም በባርነት ተረግጦ ይገዛል።

14- ነገር ግን በባርነት የሚገዛቸውን ሕዝብ እፈርድበታለሁ፤ ከዚያም ብዙ ሀብት ይዘው ይወጣሉ።

15- አንተ ግን ወደ አባቶችህ በሰላም ትሄዳለህ፤ ዕድሜም ጠግበህ ወደ መቃብር ትወርዳለህ።

16- በአራተኛውም ትውልድ ዘርህ ወደዚህ ምድር ይመለሳል፤ የአሞራውያን ኃጢአት ገና ጽዋው አልሞላምና።»

- ደግሞም እግዚአብሔር የአብራም ዘሮች ወደ ሌላ አገር ሄደው እንደሚኖሩ እና ከ400 ዓመታት በኋላም እግዚአብሔር መልሶ ወደ ከነዓን ንደሚያመጣቸው ተናገረ።

- እግዚአብሔር በአብርሃም ዘሮች ላይ የሚደርስባቸውን እንዴት አወቀ?

- እግዚአብሔር የአብርሃም ዘሮች ከመፈጠራቸው በፊት ምን እንደሚደርስባቸው ያውቃል።

- ነገ ምን እንደሚሆን ታውቃላችሁ?
- አናውቅም።

- በሚቀጥለው ወር ምን እንደሚሆን ታውቃላችሁ?
- አናውቅም።

- በሚቀጥለው ዓመት ምን እንደሚሆን ታውቃላችሁ?
- አናውቅም።

- እግዚአብሔር ግን ሁሉን ያውቃል።

- እግዚአብሔር ነገ በእኛ ላይ ምን እንደሚደርስ ያውቃል።
- እግዚአብሔር በሚቀጥለው ወር በእኛ ላይ ምን እንደሚደርስ ያውቃል።

- እግዚአብሔር በሚቀጥለው ዓመት በእኛ ላይ ምን እንደሚደርስ ያውቃል።
- ወደፊት የሚሆነውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- አብራም 99 ዓመት ሲሞላው እግዚአብሔር በድጋሚ ለአብራም ተናገረው።

ዘፍጥረት 17፥1-5

1- አብራም ዕድሜው 99 ዓመት በሆነ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ተገልጦለት እንዲህ አለው፣ «እኔ ኤልሻዳይ ነኝ፤ በፊቴ ተመላለስ፣ ነቀፋም አይኑርብህ

2- በእኔና በአንተ መካከል የተመሠረተውን ኪዳን አጸናለሁ፤ ዘርህንም እጅግ አበዛለሁ።»

3- አብራም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፣ እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፣

4- «እነሆ፤ የምገባልህ ኪዳን ይህ ነው፤ የብዙ ሕዝቦች አባት ትሆናለህ።

5- ከእንግዲህ ወዲያ ስምህ አብራም መባሉ ቀርቶ አብርሃም ይሆናል የብዙ ሕዝቦች አባት አድርጌአለሁና።»

- እግዚአብሔር አብራምን ተናገረው አዲስ ስምም ሰጠው።

- እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው አዲስ ስም ማን ነው።

- አብርሃም።

- እግዚአብሔር ለአብራም አዲስ ስም የሰጠው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም የአብራም ዘር ብዙ ሕዝብ ስለሚሆን ነው።

- እግዚአብሔር ለሦራም አዲስ ስም ሰጣት።

ዘፍጥረት 17፡15-16

15- እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ አለው፣ ሦራን ከእንግዲህ ሦራ ብለህ አትጠራትም። ስሟ ከዛሬ ጀምሮ ሣራ ይሁን።

16- እኔ እባርካታለሁ። ከእርሷም ወንድ ልጅ እሰጥሃለሁ፤ የብዙም ሕዝቦች እናት ትሆን ዘንድ እባርካታለሁ፤ የሕዝቦችም ነገሥታት ከእርሷ ይወጣሉ።»

- እግዚአብሔር ለሦራ የሰጣት አዲስ ስም ማን ነው?
- ሣራ።

- እግዚአብሔር ለሦራ አዲስ ስም የሰጣት ለምንድን ነው?
- ምክንያቱም የሦራም ዘር ብዙ ሕዝብ ስለሚሆን።

- ሣራ መካንና ያረጀች ብትሆንም እንኳ እግዚአብሔር ምን የሚል ቃል ገባላት?

- ሣራ መካንና ያረጀች ብትሆንም እንኳ እግዚአብሔር የብዙዎች እናት እንደምትሆን ቃል ገባላት።

- ሣራ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ቃል ገባላት።

- እግዚአብሔር ቃል በገባለት ጊዜ አብርሃም ምን እንዳደረገ እስቲ እንመልከት፡

ከዘፍጥረት 17፡17

17- አብርሃምም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤ ሣቀና በልቡ፣ «እንዲያው ምንስ ቢሆን የመቶ ዓመት ሽማግሌ የልጅ አባት መሆን ይችላልን? ሣራስ በዘጠና ዓመቷ ልጅ መውለድ ትችላለችን?» አለ።

- አብርሃምና ሣራ ዕድሜያቸው ስንት ነበር?
- የአብርሃም 100 የሣራ ደግሞ 90 ነበር።

- አብርሃም ለምን ሳቀ?
- አብርሃም የሳቀው በእግዚአብሔር ስላላመነ ነበር?

- አይደለም።

- ታዲያ አብርሃም ለምን ሳቀ?

- አብርሃም የሳቀው እርሱና ሣራ አርጅተው ሳለ እግዚአብሔር ልጅ ሊሰጣቸው ስለ ሆነ ነው።

- አብርሃምና ሣራ ዕድሜያቸው ስንት ነበር?

- የአብርሃም 100 የሣራ ደግሞ 90 ነበር።

- እግዚአብሔር ለ100 ዓመት ሽማግሌና ለ90 ዓመት መካን አሮጊት ወንድ ልጅ መስጠት ችሏል?

- አዎን።

- የመጀመሪያውን ሰው ማን ፈጠረው?

- እግዚአብሔር።

- የመጀመሪያዋን ሴት ማን ፈጠራት?

- እግዚአብሔር።

- ለሁሉም ሕፃን ሕይወትን የሚሰጥ ማን ነው?

- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር ሊያደርገው የማይችለው ነገር አለ?

- የለም።

- እግዚአብሔር ለ100 ዓመት ሽማግሌና ለ90 ዓመት መካን አሮጊት እንኳ ወንድ ልጅ መስጠት ይችላል።